# አኳ ፎር ኦል
# ሜኪንግ ዎተር ካውንት
# (Making Water Count)

## የድጋፍ ማመልከቻ መመሪያ 2026
## (Application Guidance 2026)

አኳ ፎር ኦል

## ክፍል 1፡ መግቢያ እና ስለ አኳ ፎር ኦል

### በውሃ እና ሳንቴሽን አገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ አነስተኛ እና መካከልኛ የንግድ ድርጅቶችን ሚና ማጠናከር

አኳ ፎር ኦል (Aqua for All) ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የውሃ እና ሳኒቴሽን መፍትሄዎችን በስፋት ለማቅረብ ዝግጁ ከሆኑ ጥቃቅን አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች (ኢንተርፕራይዞች) ጋር በትብብር ይሰራል። ከ20 ዓመታት በላይ ባካበትነው ልምድ እና ሜኪንግ ዎተር ካውንት (Making Water Count) በተሰኘው መርሃ ግብር ባዘጋጀነው ባለሁለት አቅጣጫ አካሄድ ላይ በመመስረት፤ ለመስኩ ዕድገት ተግዳሮት የሆኑ ችግሮችን በማቃለል እንዲሁም ተጨማሪ የህዝብ / መንግስት እና የግል መዋዕለ ንዋይ ፍሰት አማካኝነት የተሳላጡ የፋይናንስ ድጋፍና የሙያ እገዛ እንዲኖር እናደርጋለን።

የውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ባልተዳረሰባቸው ማህበረሰቦች ዘንድ በስፋት የመድረስ ከፍተኛ አቅም ያላቸውን ድርጅቶችን በመደገፍ፤ አካታች፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ አገልግሎቶችን ለረጅም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ጠንካራ አካባቢያዊ ግብይቶች እንዲጠናከሩ እናግዛለን።

በውሃ እና ሳኒቴሽኝ መስክ የሚሰሩ የንግድ ድርጅት ከሆኑና የድርጅትዎን ተደራሽነት ለማስፋት ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ ይህ ሰነድ ለድጋፍ መረሃግብር ማመልከቻ ለማቅረብ ሂደቱን ያመለክትዎታል፡፡

### ስለ አኳ ፎር ኦል (Aqua for All)

አኳ ፎር ኦል አካታች፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እና የሳኒቴሽን አገልግሎት ለሁሉም ሰው ተደራሽ እንዲሆን የሚሰራ ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው። ተልዕኳችን ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት የውሃ እና ሳኒቴሽን አገልግሎት ዘርፍን ለመለወጥ በግል መዋዕለ ንዋይ በመስኩ ለሚንቀሳቀሱ የንግድ ድርጅቶች (ኢንተርፕራይዞች) እንዲሰባሰብ ማድረግ ነው።

የአካባቢ የውሃ እና ሳኒቴሽን አገልግሎት በገበያ ላይ የተመሰረቱ መፍትሄዎቻቸውን እንዲያስፋፉ እና የግል መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ይህን ዘርፍ እንዲደገፍ እንሠራለን ። ለገበያ ልማት የሚውል የግል መዋዕለ ንዋይ በማንቀሳቀስ የሀብት አቅርቦትን በመጨመር፣ በተለይም በአፍሪካ እና በእስያ አህጉራት የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ የውሃ እና ሳኒቴሽን አገልግሎቶች ተደራሽነትን እናፋጥናለን።

የአገልግሎት እና የገንዘብ ክፍተቶችን በመሙላት የዘላቂ ልማት ግብ ቁጥር 6ን (ንጹህ ውኃ እና ሳኒቴሽን ለሁሉም የሚለውን መርህ) ለማሳካት፣ በገበያ ላይ የተመሰረቱ መፍትሄዎች ከህዝብ/መንግስት እና ከግል ሀብት ጋር ተቀናጅተው መቅረባቸው ወሳኝ መሆኑን እናምናለን።

ለተጨማሪ መረጃ ፡https://aquaforall.org/

## ክፍል 2፡ የምናቀርባቸው ድጋፎች

### 2.1. የምናቀርባቸው ድጋፎች

አኳ ፎር ኦል  የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ የውሃ እና ሳኒቴሽን አገልግሎቶችን በስፋት ማቅረብ የሚችሉ እና ለውጥ ማምጣት ላይ ትኩረት ያደረጉ  ንግድ ድርጅቶችን (ኢንተርፕራይዞችን) ይፈልጋል።

ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች  በሙያ፣ በፋይናንስ እና በሥራ አመራር ረገድ ራሳቸውን እንዲችሉ እንደ ፍላጎታቸው የተቃኘ ድጋፍ እንሰጣለን። ራዕያችን  በመስኩ የአካባቢው ተዋናዮች አገልግሎቱን ማስፋፋት እና ዘላቂ ማድረግ የሚችሉበት የበለፀገ የውሃ እና ሳኒቴሽን ዘርፍን ማየት ነው።

## 2.2. ለድጋፍ ብቁ ለመሆን ሚስፈልጉ መስፈርቶች

ድጋፉን ለማግኘት ማመልከት የሚፈልጉ ከሆነ ተነሳሽነትዎ ከመርሃ ግብራችን (ፕሮግራማችን) ጋር መጣጣሙን በሚከተሉት ነጥቦች ያረጋግጡ፡-

1. ስራው በአሁኑ ወቅት ክፍት ከሆኑት የድጋፍ ማመልከቻ የጥሪ ማስታወቂያዎች ከአንዱ ጋር የተገናኘ መሆን አለበት። እባክዎን ወቅታዊ ጥሪዎችን ለማየት ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ። እያንዳንዱ አህጉራዊ ጥሪ ተጨማሪ መስፈርቶች ወይም ትኩረት የሚሰጣቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሊኖሩት ይችላሉ።
2. ድጋፉ የሚከተሉትን አነስተኛ መስፈርቶችን ለሚያሟላ ማህበራዊ ድርጅት ወይም የንግድ ተቋም መሆን አለበት፡-

   ሀ. የተመዘገበ/ፈቃድ ያለው እና ቢያንስ ለ 2 ዓመታት የሰራ

   ለ. ግልጽ የሆነ የለውጥ ተልዕኮ ያለው እና ለዘላቂ ልማት ግብ 6 ስኬት አስተዋጽኦ የሚያደርግ (ከታች ነጥብ 3ን ይመልከቱ)፤

   ሐ. እኛ ትኩረት በምናደርግባቸው ሀገራት ወይም ክፍለ አህጉራት ውስጥ የሚንቀሳቀስ (ከታች 4ኛ ተ.ቁ ይመልከቱ)፤

   መ. በዋና ምርቶቹ እና አገልግሎቶቹ ቢያንስ የፅንሰ-ሃሳብ ማረጋገጫ (proof-of-concept) ደረጃ ላይ የደረሰ፤

   ሠ. የውሃ እና ሳኒቴሽን ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን በንግድ እና/ወይም በገበያ ላይ በተመሰረተ አሰራር የሚያቀርብ፤

   ረ. በፋይናንስ ራሱን የቻለ ወይም ራሱን ለመቻል ግልጽ እቅድ ያለው።

3. **ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ፡-**

አኳ ፎር ኦል በዋናነት ደህንነቱ የተጠበቀ የመጠጥ ውሃ እና የሳኒቴሽን አገልግሎት ተደራሽነት ላይ በማተኮር፣ ለዘላቂ ልማት ግብ 6 (SDG 6) ስኬት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ድርጅቶችን ይደግፋል። እንደየ ሀገሩ ወይም ክፍለ አህጉሩ ሁኔታ ተጨማሪ የትኩረት አቅጣጫዎች ሊኖሩት ይችላሉ፤ ይህም በየጊዜው በሚወጡ የማመልከቻ የጥሪ ማስታወቂያዎች ላይ ይገለጻል።

### በመጠጥ ውሃ

- ✔ ደህንነቱ የተጠበቀ ውሃ የሚያቀርቡ ድርጅቶች
- ✔ የቤት ውስጥ የውሃ ማጣሪያ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማከማቻ አገልግሎት የሚሰጡ
- ✔ የጥገና እና የእለት ተዕለት የሥራ ማከናወኛ አገልግሎቶች

✔ ዘመናዊ የውሃ ቴክኖሎጂ አቅራቢዎች (የውሃ ቆጣሪ፣ የክፍያ ሥርዓት፣ ኮምፒውተር ተጠቃሚ መረጃና የግንኙነት ዘዴዎች እንዲሁም የመሳሰሉት)

✔ የመሠረተ ልማት እና የቁሳቁስ አቅራቢዎች (ለምሳሌ፡- የውሃ ቁፋሮ፣ የስርጨት አገልግሎት፣ የቁሳቁስ ምርት እና ስርጭት)

✔ ሌሎች የውሃ ስርጭት አማራጮች (በቦቴ መኪና የውሃ አቅርቦት)

## በሳኔቴሽን

✔ የመጸዳጃ ቤት ኢኮኖሚ(Toilet Economy) አገልግሎት አቅራቢዎች( በሳኔቴሽን እሴት ሰንሰለት ውስጥ ምርቶችንና አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ንግዶች፣ ድርጅቶች እና ተቋማት ናቸው። እነዚህ አገልግሎት ሰጪዎች ከመጸዳጃ ቤት ግንባታና ግብአት ማምረት ጀምሮ እስከ እዳሪ / ሰገራ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ እና ማጣራት ድረስ በሰንሰለቱ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ላይ ይሚሳተፉትን ያጠቃልላል)

✔ የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ (መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ እና ማከም) ሥራ ላይ ያሉ

✔ ሀብት መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እና የሰው ልጅ ፍሳሽ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ የሚያውሉ አገልግሎቶች

እንደ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋም እና የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ባሉ ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችን (ኢንተርፕራይዞችን) በተለየ ሁኔታ እናበረታታለን።

አኳ ፎር ኦል ትኩረቱን ጠንካራ ኢንተርፕራይዞችን በመገንባት የገበያ ለውጥ ማምጣት ላይ ቢያደርግም፣ በዘርፉ ሥነ-ምህዳር ላይ ሰፋ ያለ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ አነቃቂ ተነሳሽነት ያላቸው ኢንተርፕራይዞችም ማመልከት ይችላሉ።

## ክፍል 3: **ትኩረት በምናደርግባቸው አካባቢዎች**

- **ምስራቅ አፍሪካ** (በተለይም ኢትዮጵያ፣ ኬንያ እና ዩጋንዳ)
- **ምዕራብ አፍሪካ** (በተለይም ሴኔጋል እና ጋና)
- **ደቡብ እስያ** (በተለይም ካምቦዲያ፣ ኢንዶኔዥያ እና ቪየትናም)
- **መካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ** (በተለይም ዮርዳኖስ እና ግብፅ)

አኳ ፎር ኦል (Aqua for All) ከላይ ካልተጠቀሱ ሀገራት ለሚመጡ ጥያቄዎችም የማመለከቻ የጥሪ ማስታወቂያ ሊያወጣ ይችላል። የእርስዎ ድርጅት (ኢንተርፕራይዝ) በአሁኑ ወቅት በእነዚህ አካባቢዎች የማይገኝ ከሆነ፣ የወደፊት ጥሪዎችን ለማየት ድረ-ገጻችንን ወይም ሊንክድኢን (LinkedIn) ገጻችንን ይከታተሉ።

በመስኩ ለሚደረገው ጥረት ተነሳሽነቱን እንደየ አካባቢው ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ለማስቀጠል የሚያስችል ግልጽ እቅድ ያለው መሆን እና በአኳ ፎር ኦል የፕሮጀክት ቆይታ ጊዜም ሆነ ይህ ድጋፍ ካበቃ በኋላ ሌሎች የደጋፍ/ሀብት ምንጮችን እንዴት መሳብ እንደሚቻል ላይ ጠንካራ ትኩረት ሊኖር ይገባል።

## ክፍል 4: የድጋፍ ዘርፍ (Our Instruments)

እንደየ ድርጅቶቹ የዕድገት ደረጃ እና ፍላጎት የምንሰጣቸው የተለያዩ የድጋፍ ዘርፎች አሉን። እነዚህ የድጋፍ ዘርፎች ለእያንዳንዱ ድርጅት ተገቢውን እና የተቃኘ ድጋፍ ለመስጠት ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። በመሆኑም እያንዳንዱ የድጋፍ ዘርፍ የራሱ የሆነ መስፈርት፣ የገንዘብ መጠን እና አደረጃጀት አለው።

ከዚህ በታች ስለ ድጋፍ ዘርፍ አጠቃላይ መግለጫ ቀርቧል። ለእርስዎ ኢንተርፕራይዝ ፍላጎት እና እቅድ የትኛው ይበልጥ እንደሚስማማ ለመረዳት እያንዳንዱን የድጋፍ ዘርፍ በዝርዝር መመልከት ይችላሉ።

ለአንድ የተወሰነ የድጋፍ ዘርፍ ፍላጎት ካለዎት፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን የማመልከቻ ምክሮች ልብ ይበሉ። አኳ ፎር ኦል በምዝገባው ሂደት ውስጥ ከድርጅቱ (ከኢንተርፕራይዙ) ጋር በመመካከር ይበልጥ ተገቢ የሆነውን የድጋፍ ዘርፍ ይወስናል (ለተጨማሪ ዝርዝር ቀጣዩን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)።

| **መሣሪያ** (Instrument) | **በስኬት ምዕራፍ ላይ የተመሰረተ ድጋፍ** (Milestone-Based Grant) | **በውጤት ላይ የተመሰረተ ድጋፍ** (Results-Based Grant) | **የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻ** (SIINC) | **የሙያ ድጋፍ** (Technical Assistance) |
|---|---|---|---|---|
| **ትርጉም** | ክፍያ የሚፈጸመው አስቀድሞ ስምምነት የተደረሰባቸው የተወሰኑ የሥራ ምዕራፎች ወይም ተግባራት ሲጠናቀቁ የሚሰጥ የድጋፍ ዓይነት ነው። | ክፍያ የሚፈጸመው አስቀድሞ የተወሰኑ ውጤቶች ሲመዘገቡ ነው። ውጤቶቹ ከድርጅቱ ዕድገት ወይም የንግድ ግቦች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፤ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊትም በሦስተኛ ወገን ይረጋገጣሉ። | ክፍያ የሚፈጸመው ለተመዘገቡ ተጨማሪ የማኅበራዊ ተፅዕኖ ውጤቶች ነው። መለኪያዎቹ አስቀድመው የሚወሰኑ ሲሆን፣ የተገኙት ውጤቶች ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በሦስተኛ ወገን ይረጋገጣሉ። | ለክህሎት ልማት፣ ለእውቀት ሽግግር እና/ወይም ለልዩ ፍላጎቶች አማካሪ ለመቅጠር የሚመደብ ሀብት። |
| **የጊዜ ገደብ *** | ከ18–36 ወራት | ከ18–36 ወራት | ከ24–36 ወራት | ከ3–12 ወራት |
| **የገንዘብ መጠን*** | ከ50,000 – 250,000 ዩሮ | ከ150,000 – 300,000 ዩሮ | ከ150,000 – 400,000 ዩሮ | ከ20,000 – 100,000 ዩሮ |
| **የፕሮጀክት ምሳሌ** | አንድ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ጣቢያ ትርፋማነቱን ለማሳደግ ቆሻሻን ወደ እሴት | አንድ ድርጅት የውሃ ማከፋፈያ ኪዮስኮችን ያስተዳድራል። ትርፋማ ለመሆን እና ለዕድገት | አንድ የንጹሕ ውኃ ድርጅት በገጠር አካባቢዎች የቧንቧ ውኃ ያቀርባል። ዝቅተኛ ገቢ | አንድ በኮንቴይነር ላይ የተመሰረተ የጽዳት ድርጅት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የሚቀይሩ ምርቶችን በሙከራ ደረጃ ሠርቷል። ሙከራው ሲሳካ፣ ድርጅቱ የምርቱን እና የምርቱን ሽያጭ ለማስፋፋት የገንዘብ ድጋፍ ይፈልጋል። ፕሮጀክቱ የሠራተኞችን አቅም መገንባት እና ከባለሥልጣናት ጋር መተባበርን ያካትታል። | የሚሆን ካፒታል ለማግኘት፣ የኪዮስኮቹን ሽያጭ ማሳደግ አለበት። ድጋፉ ሽያጩ የታለመው ደረጃ ላይ ሲደርስ ክፍያ በሚፈጸምበት መንገድ የተቀረጸ ነው። ድርጅቱ ውጤቱን ለማምጣት በሚያደርጋቸው ተግባራት ላይ ገደብ አይደረግበትም። | ያላቸው ቤተሰቦች በከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጪ ምክንያት አገልግሎቱን አያገኙም። **የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻ መርሃግብር** ድርጅቱ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ደንበኞች ቁጥር ሲጨምር ሽልማት እንዲሰጠው ተደርጎ የተቀረጸ ነው። ይህም ድርጅቱ ከፍተኛውን መዋእለ ንዋይ እንዲሸፍን እና የደንበኞቹን ቁጥር እንዲያሰፋ ይረዳዋል። | ውሳኔ ለመስጠት እና ተፅዕኖውን ለማሳየት የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓቱን ማሻሻል ይፈልጋል። 'አኳ ፎር አል' አንድ የውጭ አካል የድርጅቱን ነባራዊ ሁኔታ አጥንቶ አዲስ ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው ድጋፍ ያደርጋል። |

* **የጊዜ ገደብ እና የገንዘብ መጠን እንደ ግምት የቀረቡ ሲሆን፣ እንደ ድርጅቱ ፍላጎት እና በረበው ምክረ ሃሳብ መሠረት ከ'አኳ ፎር አል' ጋር በጋራ የሚወሰኑ ይሆናል።**

## በስኬት ምዕራፍ ላይ የተመሰረቱ የገንዘብ ድጋፎች (Milestone-Based Grants)

### ትርጉም፡-

በስኬት ምዕራፍ ላይ የተመሰረቱ የገንዘብ ድጋፎች የንግድ ድርጅቶችን የንግድ፣ የፋይናንስ እና የሥራ አፈጻጸም ለማሻሻል የታለሙ፣ ክፍያቸውም የተወሰኑ የሥራ ምዕራፎች ወይም ውጤቶች ሲከናወኑ የሚፈጸምባቸው የገንዘብ ድጋፍ ዘርፍ ነው። በውጤት ላይ ከተመሰረቱ ድጋፎች በተለየ መልኩ፣ የሥራ እንቅስቃሴዎች እና የፋይናንስ ዕቅዶች ከውል ስምምነት በፊት የሚወሰኑ ሲሆን፣ ሪፖርታቸውም በየሥራ እንቅስቃሴ ደረጃው ለ'አኳ ፎር አል' ይቀርባል።

### አሠራሩ እንዴት ነው?

'አኳ ፎር አል' ከድርጅቱ ጋር በመሆን ለዚህ የድጋፍ ዘርፍ ብቁ መሆኑን ይወስናል። ድርጅቱ ከውል ስምምነቱ በፊት ለሥራው የሚያስፈልጉ ዝርዝር ተግባራትን፣ የሥራ አመክንዮን እና ዝርዝር በጀትን ይነድፋል። በዚህ ዕቅድ ላይ

በመመስረት፣ ድርጅቱ ሥራዎችን ለመጀመር የሚያስችለውን ቅድመ ክፍያ ያገኛል። ቀሪዎቹ ክፍያዎች የሚፈጸሙት አስቀድሞ የተስማማባቸው የሥራ ምዕራፎች ወይም ውጤቶች ሲሳኩ ነው (በተለይም በየ6 ወሩ)።

### ይህ ድጋፍ ለማን ነው?

ይህ ድጋፍ  በማደግ ምዕራፍ ላይ ላሉና  አስቀድመው አሰራራቸውን ላሳለጡ  ድርጅቶች ተስማሚ ነው። እነዚህ ድጋፎች ስኬትን ይበልጥ ለማሳደግ እና ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ አሰራሮችን ለማስፋፋት እንዲቻል፣ ከድርጅቱ የራሱ ግቦች (ወይም ከሌሎች ፕሮጀክቶች) ጋር ሊጣጣሙ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በውጤት ላይ የተመሰረቱ ድጋፎች አንድ ድርጅት ኢንቨስትመንትን የመቀበል ብቃትና ብስለት እንዳለው ለባለሀብቶችና ለአበዳሪዎች ማሳያ ሆነው ያገለግላሉ።

### መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

- ✔ የቅድመ ክፍያ አስፈላጊነት ማረጋገጫ (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ)
- ✔ የሥራ ሂደት ወይም የሥራ አፈጻጸም ማሻሻያ ግልጽ ፍላጎት (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ)
- ✔ ዝግጁ የሆነ የፋይናንስ አስተዳደር እና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት

### የማመልከቻ  ጠቃሚ ምክሮች

ማመልከቻዎ በሥራው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማሳካት ባቀዷቸው ተግባራት እና ግቦች ላይ ማተኮር አለበት፤ እንዲሁም እነዚህ ተግባራት ከድርጅትዎ የዕድገት ዕቅድ ጋር እንዴት እንደሚጣጣሙ ማሳየት ይኖርበታል።

## በውጤት ላይ የተመሰረቱ የገንዘብ ድጋፎች (Results-Based Grants)

### ትርጉም፦

በውጤት ላይ የተመሰረቱ የገንዘብ ድጋፎች፣ ክፍያ የሚፈጸመው አስቀድሞ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው ውጤቶች መከናወናቸው ሲረጋገጥ ነው። እነዚህ ድጋፎች ውጤቶቹን ለማምጣት የሚያስችል ተለዋዋጭነትን (Flexibility) ለማቻቻል የታለሙ ሲሆን፣ የፋይናንስ ድጋፉን ከሥራ እንቅስቃሴዎች ይልቅ ከተረጋገጠ ስኬት ጋር ያቆራኙታል።

### አሠራሩ እንዴት ነው?

'አኳ ፎር ኦል' ከድርጅቱ ጋር በመሆን የድጋፍ ጥያቄ ማመልከቻው  ለዚህ ድጋፍ ብቁ መሆኑን ይለያል። ድርጅቱ ለውጤት ተኮር ድጋፍ ከተመረጠ፣ ክፍያ የሚፈጸምባቸው 2-4 የሚሆኑ መለኪያዎችን ከ'አኳ ፎር ኦል' ጋር በጋራ ይወስናሉ። እነዚህ መለኪያዎች ከድርጅቱ የዕድገት እና የተፅዕኖ ግቦች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው (ለምሳሌ፦ የአዳዲስ ደንበኞች ቁጥር)።

በየጊዜው (በተለይም በየዓመቱ)፣ ገለልተኛ ሶስተኛ አካል በእነዚህ መለኪያዎች ላይ የታየውን መሻሻል ይገመግማል። ለእያንዳንዱ መለኪያ የተቀመጠው ዝቅተኛ ውጤት ከተገኘ፣ የውጤት ክፍያው ይፈጸማል።

## ይህ ድጋፍ ለማን ነው?

በውጤት ላይ የተመሰረቱ የገንዘብ ድጋፍ ሥራቸውን በሚገባ ላስጀመሩ እና  በዕድገት ላይ ላሉ ድርጅቶች ተመራጭ የድጋፍ ዘርፍ ነው። ስኬትን ለማጉላት እና የተረጋገጡ አሠራሮችን ለማስፋፋት ከድርጅቱ የራሱ ግቦች (ወይም ሌሎች ፕሮጀክቶች) ጋር ሊጣጣሙ ይችላሉ። በተጨማሪም እነዚህ ድጋፎች ድርጅቱ መዋዕለ ንዋይ ፍሰት የመቀበል ብቃት እና ብስለት እንዳለው ለኢንቨስተሮች ማሳያ ይሆናሉ።

## መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

- ✔ የ3+ ዓመታት የንግድ የሥራ ልምድ
- ✔ የውጤት መለኪያዎችን ለመከታተል እና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት

## ልብ ይበሉ፡-

- ✔ በውጤት ላይ የተመሰረቱ ድጋፎች ድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል በቂ የፋይናንስ አቅም እንዲኖረው ይፈልጋሉ። ስለዚህ ሥራዎችን ለመጀመር ቅድመ ድጋፍ ለሚፈልጉ ድርጅቶች ተስማሚ አይደሉም።
- ✔ ሁሉም ግቦች ከዚህ የድጋፍ መዋቅር ጋር ሊጣጣሙ አይችሉም ። ለምሳሌ፡- ውጤታቸው ወይም የጊዜ ገደባቸው እርግጠኛ ያልሆኑ (እንደ አዲስ ምርት መሞከር፣ ምርምር እና ልማት፣ የውትወታ ሥራዎች) ወይም ውጤታቸው በሁለት አማራጭ ብቻ የሚለካ (ለምሳሌ፡- የሽርክና ስምምነት መፈረም፣ የካርቦን ክሬዲት የምስክር ወረቀት ማግኘት)።

## የማመልከቻ  ጠቃሚ ምክሮች

ለድጋፍ ሲያመለክቱ ስለ ፕሮጀክቱ ያቀዱትን ዝርዝር የሥራ ዕቅድ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን፣ በተጨማሪም ስለ ድርጅትዎ አጠቃላይ የዕድገት ግቦች ፍንጭ መስጠት ይችላሉ።

## የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች (Social Impact Incentives - SIINCs)

## ትርጉም፡-

**የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች** አስቀድሞ የተወሰኑ እና በገለልተኛ አካል የተረጋገጡ ውጤቶችን ለሚያስመዘግቡ ተፅዕኖ-ፈጣሪ ድርጅቶች ለተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ የገንዘብ ሽልማት ነው። ድርጅቶች ተጨማሪ ገቢ በማግኘት ትርፋማነታቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ፤ ይህም ለዕድገታቸው የሚሆን ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ ለመሳብ ይረዳቸዋል። **ለማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻ ድጋፍ** ብቁ ለመሆን፣ ድርጅቶች ከዚህ ጎን ለጎን የሚመለስ የመዋዕለ ንዋይ ገንዘብ (Repayable investment) ማሰባሰብ ይኖርባቸዋል። የመዋእለ ንዋይ ፍሰቱ ዓይነት የተለያየ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፡- ባለቤትነት፣ ብድር ወይም መካከለኛ)

## አሠራሩ እንዴት ነው?

'አኳ ፎር አል' እና ድርጅቱ የማበረታቻ ክፍያውን የሚያስጀምሩ የማኅበራዊ ተፅዕኖ መለኪያዎች ላይ ይስማማሉ። እነዚህ መለኪያዎች ከድርጅቱ መሠረታዊ ግቦችና የንግድ ሞዴል ጋር የተጣጣሙ ሆነው፣ ያለዚህ ድጋፍ ሊመጡ የማይችሉ ተጨማሪ ተፅዕኖዎችን በመፍጠር ላይ ያተኩራሉ።

ስምምነቱ እንደተፈረመ፣ ድርጅቱ መደበኛ ሥራዎቹን ያከናውናል። አስቀድሞ በተቀመጡ የጊዜ ገደቦች (በተለምዶ በየዓመቱ)፣ ገለልተኛ ታዛቢ የተስማሙባቸው የማኅበራዊ ተፅዕኖ መለኪያዎች መሳካታቸውን ያረጋግጣል። የተረጋገጡት ውጤቶች ሲመዘገቡ፣ 'አኳ ፎር አል' ለድርጅቱ የማበረታቻ ክፍያ ይፈጽማል።

እነዚህ ማበረታቻዎች ከመደበኛ ሽያጭ ገቢ በተጨማሪ የሚከፈሉ በመሆናቸው፣ የድርጅቱን ትርፋማነት ይጨምራሉ፤ እንዲሁም በመስኩ መዋዕለ ንዋይ ለሚያፈሱ ይበልጥ ተመራጭ እንዲሆን ያደርጉታል።

## ይህ ድጋፍ ለማን ነው?

**የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች** በንግድ ረገድ ውጤታማ ፣ተፅዕኖ-ተኮር ለሆኑ እና ለዕድገት ዝግጁ ለሆኑ ድርጅቶች ተስማሚ ነው። በተለይ የሚከተሉት ላሏቸው ድርጅቶች የተሻለ ነው፡-

- ✔ የተረጋገጠ የንግድ ሞዴል እና ግልጽ የዕድገት ጉዞ
- ✔ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊለኩ እና ሊረጋገጡ የሚችሉ የተፅዕኖ መለኪያዎች
- ✔ ጠንካራ የደንበኞች መረጃ

## መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

- ✔ የ3+ ዓመታት የንግድ የሥራ ልምድ
- ✔ ቢያንስ 500,000 ዩሮ የሚመለስ ኢንቨስትመንት (ባለቤትነት ወይም ብድር) ማሰባሰብ
- ✔ ወጪን የሸፈነ/ትርፋማ የሆነ ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርፋማ ለመሆን ግልጽ ዕቅድ ያለው
- ✔ የተመዘገበ የተፅዕኖ ታሪክ እና የተዘረጋ የተፅዕኖ መለኪያ ሥርዓት

## ልብ ይበሉ፡-

✔**የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች** ለሥራ ማስኬጃ የቅድመ ክፍያ ለሚፈልጉ ድርጅቶች ተስማሚ አይደለም።

✔ እርግጠኛ ባልሆኑ ግቦች (ለምሳሌ፡- አዲስ ምርት መሞከር፣ የማሳመኛ/ውትወታ ሥራዎች) ወይም ውጤታቸው በሁለት አማራጭ ብቻ ለሚለካ (ለምሳሌ፡- የሽርክና ስምምነት መፈረም) ውጤታማነቱ አነስተኛ ነው።

### የማመልከቻ ጠቃሚ ምክሮች

ዝርዝር የፕሮጀክት ዕቅድ ከማቅረብ ይልቅ፣ ድርጅቶች በሚከተሉት ላይ እንዲያተኩሩ ይበረታታሉ፡-

✔ **የተፅዕኖ ምኞትዎ፡-** ምን ምን ተጨማሪ ማኅበራዊ ውጤቶችን ለማምጣት

✔ **የተፅዕኖ መለኪያ እና አመራር ሥርዓትዎ መግለጫ፡-** በአሁኑ ወቅት ተፅዕኖዎ እንዴት እንደሚለካ እና እንደሚረጋገጥ

✔ **የፋይናንስ እጥረት ያለባቸው ዘርፎች፡-** ለምሳሌ ተጨማሪ ተፅዕኖ መፍጠር ትርፋማነትን የሚቀንስባቸው ወይም ተጨማሪ ሀብት የሚጠይቅባቸው ሁኔታዎች

ይህ አቀራረብ **የማኅበራዊ ተፅዕኖ** ማበረታቻዎችን ከድርጅቱ ነባራዊ ግቦች እና ተግዳሮቶች ጋር ለማጣጣም ግልጽ የሆነ ምክክርና ውይይት ለማድረግ ያስችላል።

**በውጤት ላይ በተመሰረተ የገንዘብ ድጋፍ እና የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

በውጤት ላይ የተመሰረቱ የገንዘብ ድጋፎች እና የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች ብዙ ተመሳሳይነቶች አሏቸው፤ ሁለቱም በውጤት ላይ የተመሰረቱ የድጋፍ ዓይነቶች ናቸው። ይህም ማለት 'አኳ ፎር ኦል' ለድርጅቱ የተወሰኑ የሥራ ተግባራትን ወይም የፋይናንስ ግዴታዎችን አያዝዝም፤ ይልቁንም ክፍያዎችን የሚፈጽመው በተረጋገጡ ስኬቶች ላይ ተመስርቶ ነው። ሆኖም ግን፣ ጥቂት መሠረታዊ ልዩነቶች አሏቸው፡-

1. **የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻ** ትኩረት የሚያደርገው በተፅዕኖ (Impact) ነክ ውጤቶች ላይ ብቻ ነው። በአንፃሩ **በውጤት ላይ የተመሰረቱ የገንዘብ ድጋፎች** እንደ ድርጅቱ የዕድገት ግቦች ሰፋ ያሉ ውጤቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ምንም እንኳን በውጤት ላይ የተመሰረቱ ድጋፎች ትኩረታቸው በተፅዕኖ ላይ ብቻ ባይሆንም፣ ድርጅቶቹ አሁንም ከ'አኳ ፎር ኦል' የተፅዕኖ ደረጃዎች እና ከዘላቂ ልማት ግብ ቁጥር 6 ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው።
2. የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች እና በውጤት ላይ የተመሰረቱ ድጋፎች የተለያዩ የመምረጫ መስፈርቶች አሏቸው፤ ይህም የሚመለስ የኢንቨስትመንት ካፒታል (Repayable finance) የማሰባሰብ ግዴታን እና ነባር የተፅዕኖ መለኪያ እና አመራር ሥርዓት መኖርን ያካትታል።
3. የማኅበራዊ ተፅዕኖ ማበረታቻዎች የሚመለከተው የረጅም ጊዜ ተፅዕኖ ውጤቶችን ብቻ ነው። በውጤት ላይ የተመሰረቱ ድጋፎች ግን ለአጭር ጊዜ ውጤቶች እና ለረጅም ጊዜ ተፅዕኖዎች ክፍያ ሊፈጽሙ ይችላሉ።

### **የሙያ ድጋፍ** (Technical Assistance)

### ትርጉም፡-

የሙያ ድጋፍ  ማለት ዘላቂ የንግድ ዕድገትን ለመደገፍ፣ የኢንቨስተሮችን ፍላጎት ለመጨመር እና/ወይም ተፅዕኖን ለማሳደግ ታስቦ ለክህሎት ልማት፣ ለእውቀት ሽግግር እና ለተወሰኑ ፍላጎቶች አማካሪ ለመቅጠር (ብዙውን ጊዜ በሦስተኛ ወገን በኩል) የሚመደብ ሀብት ነው።

### አሠራሩ እንዴት ነው?

ድርጅቱ እና 'አኳ ፎር ኦል' በጋራ በመሆን የሙያ ድጋፉን አስፈላጊነት እና ትኩረት ይለያሉ። በድርጅቱ ልዩ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት (ለምሳሌ፡- የፋይናንስ አስተዳደር፣ የሥራ ቅልጥፍና፣ የንግድ አሰራር/ሞዴል ማሻሻያ ወይም የተፅዕኖ ልኬት) ድርጅቱ የሥራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለ'አኳ ፎር ኦል' ያቀርባል።

'አኳ ፎር ኦል' እና የንግድ ድርጅቱ በጋራ በመሆን የሙያ ድጋፍ ሰጪውን ይመርጣሉ። አቅራቢው አብዛኛውን ጊዜ 'አኳ ፎር ኦል' አስቀድሞ ከመዘገባቸው ነፃ ባለሙያዎች ወይም አማካሪ ድርጅቶች ይሆናል፤ አልፎ አልፎም ከእነዚህ ውጭ ሊመረጥ ይችላል። እንደ በጀቱ መጠን የጨረታ ሂደት ሊኖር ይችላል።

የሙያ ድጋፍ ዕቅዱ አቅራቢው ከመታወቁ በፊት ወይም በኋላ ሊዘጋጅ ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ድርጅቱ ዕቅዱን ለብቻው ያዘጋጃል፤ በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ ከአቅራቢው ጋር በመተባበር የሥራውን ዝርዝር እና የሚጠበቀውን ውጤት በግልጽ ያስቀምጣሉ።

እንደ ሁኔታው፣ የጸደቀው የገንዘብ ድጋፍ ለድርጅቱ ይሰጣል ወይም 'አኳ ፎር ኦል' በቀጥታ ለአቅራቢው ክፍያ ይፈጽማል።

### ይህ ድጋፍ ለማን ነው?

ልዩ የሙያ ምክር ወይም ሰፋ ያለ የክህሎት አቅም ግንባታ ለሚፈልጉ ድርጅቶች ጠቃሚ ነው። በማንኛውም የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ድርጅቶች ሊተገበር ይችላል።

### ልብ ይበሉ፡-

በአጠቃላይ የሙያ  ድጋፍ ለብቻው የሚሰጥ ሳይሆን፣ ከሌላ የገንዘብ ድጋፍ መሣሪያ መርሃ ግብሩ ጎን ለጎን ወይም እንደ ዝግጅት የሚሰጥ ነው።

### መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

- ✔ ለቴክኒክ ድጋፍ ትግበራ ወጪ ጥቂት ድርሻን በጋራ የመሸፈን  ፍላጎት እና አቅም ማሳየት። (በጋራ ፈንድ ስለማድረግ በቀጣይ ይመልከቱ)
- ✔ የቴክኒክ ድጋፉ ውጤቶች ከዚህ ፕሮጀክት ባለፈ ለሌሎች ተግባራትም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲላመዱ ተደርገው መቀረጽ አለባቸው።

### የማመልከቻ ምክሮች

በዕቅድዎ ውስጥ እነዚህን ያረጋግጡ፡-

✔ የድጋፉ መጠን እና ትኩረት ከድርጅቱ አቅም፣ ከፋይናንስ ጥንካሬው እና ድጋፉን ለመጠቀም ካለው ዝግጁነት ጋር የተመጣጠነ መሆኑን

✔ ድርጅቱ ይህ ድጋፍ ባይኖር ሊያገኛቸው የማይችላቸውን አዳዲስ ክህሎቶች፣ መሣሪያዎች ወይም ዕውቀቶች በመጨመር ተጨማሪ እሴት የሚፈጥር መሆኑን

## ክፍል 5፡ የጋራ የገንዘብ ምንጭ (Co-Funding) እና ተጨማሪ ፋይናንስ የመሳብ መስፈርቶች

ከ'አኳ ፎር ኦል' የገንዘብ ድጋፍ ጎን ለጎን፣ አመልካቾች ወይም አጋሮቻቸው የገንዘብ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። ይህ የጋራ ገንዘብ ለዚሁ ፕሮጀክት ትግበራ ብቻ መዋል አለበት።

የጋራ የገንዘብ ምንጭ በዓይነት የሚደረግ አስተዋጽኦን (ለምሳሌ፡- በሥራው ላይ የዋለ ጊዜ ወይም መሣሪያዎች) ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ አስተዋጽኦን (የግል ካፒታል፣ ድጎማ ወይም የህዝብ ገንዘብ) ሊያካትት ይችላል።

ዓላማችን የድጋፍ ገንዘብን በመጠቀም የግል እና የመንግሥት /የህዝብ ፋይናንስን ወደ ውኃና ሳኒቴሽን ዘርፍ ማሳብ ስለሆነ፣ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጮችን እንዴት ለመሳብ እንዳቀዱ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

## ክፍል 6፡ የድጋፍ ቅድመ ሁኔታዎች እና የመምረጫ መርሆዎች

### 6.1: የድጋፍ ቅድመ ሁኔታዎች (Eligibility Requirements)

አመልካቾች ከ'አኳ ፎር ኦል' ጋር አብሮ ለመሥራት የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-

1. ሕጋዊ ምዝገባ ያለው ድርጅት መሆን (ግለሰብ መሆን አይቻልም)
2. በፕሮጀክቱ ውስጥ ሃይማኖታዊ ወይም ሚሲዮናዊ ይዘት አለመኖሩ።
3. ማንኛውንም ዓይነት ማጭበርበር፣ ሙስና ወይም ተገቢ ያልሆነ ባህሪ ለመከላከል ተገቢውን እርምጃ መውሰድ።
4. ፕሮጀክቱ ሰብዓዊ መብቶችን፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ባገናዘበ የሥነ-ምግባር መንገድ እንዲሠራ ኃላፊነት መውሰድ።
5. የመረጃን ማጋራት መመሪያን (Open-source policy) መቀበል እና የተገኙ ልምዶችን ለቡድናችን እና ለውጭ አጋሮች ለማካፈል ፈቃደኛ መሆን።
6. በ'አኳ ፎር ኦል' የክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ መሠረት መረጃዎችን መሰብሰብ እና ማጋራት።

ለበለጠ መረጃ የ'አኳ ፎር ኦል' የሥነ-ምግባር መመሪያን ይመልከቱ (Code of Conduct)

### 6.2. ማመልከት የሚቻለው መቼ ነው?

አዳዲስ የድጋፍ ማመልከቻ ጥሪዎችን ለማየት ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ። ድርጅትዎ በምንሠራባቸው አገራት ውስጥ የሚገኝ ሆኖ ክፍት ጥሪ በሌለበት ጊዜ፣ ለወደፊት ግምት ውስጥ እንዲገባ የመረጃ ቅጻችንን (Intake form) መሙላት ይችላሉ።

### 6.3 .ማን ማመልከት ይችላል?

ማንኛውም በሕግ የተመዘገበ አካል ማመልከት ይችላል። ሆኖም ግን፣ ዋናው አመልካቾች የግል ንግድ ድርጅቶች (Enterprises) ከሆኑ ማመልከቻቸው ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

አኳ ፎር አል ጠንካራ አካባቢያዊ ትብብር ለሚታየባቸው ተግባራት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ የተለያዩ አይነት አጋሮችን (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የንግድ ድርጅቶችን፣ የእውቀት ተቋማትን፣ መንግስታትን፣ የአካባቢ አስተዳደሮችን) ያቀፈው ጥምረት ማመልከቻን ያበረታታል። ነገር ግን ሰራዎቹ የግሉ ሴክተርን ማሳደግ እና ማጠናከር ላይ ማተኮር አለባቸው። ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰራዎቹ በዋናነት በግሉ ዘርፍ ተዋናዮች/ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች መተግበር አለባቸው።

ከአኳ ፎር ኦል ጋር ለሚሰጥ ድጋፍ እያንዳንዱ አመልካች በውል ተጠያቂ እንዲሆን መሪ አካል መምረጥ አለበት። መሪ አካል የአኳ ፎር ሶል ፈንዶችን ብቸኛ ፈራሚ እንዲሁም ለኮንትራት ግዴታዎች ተጠያቂ ይሆናል። ውል ከመግባታችን በፊት በመሪ አካል ላይ ተገቢውን ግምገማ እናከናውናለን።

### 6.3. ትምህርት እና ልምድ መለዋወጥ (Learning)

የራሳቸውን ስኬት ለመገምገም ቁርጠኛ የሆኑትን እና ከተሞክሯቸው የሚማሩ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ስራዎችን እንደግፋለን። ይህም ከቡድናችን እና ከውጭ አጋሮቻችን ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ትምህርቶች ለመካፈል እንዲሁም የተሻለ ለመማር እና በተለይም የሴክተር ተግዳሮቶችን ለማሸነፍ እና እድገትን ለማጎልበት እንዲረዳ ታስቦ መሰራት አለበት።

በዚህ ምክንያት ከክትትልና ግምገማ ማዕቀፋችን ጋር በተጣጣመ መልኩ መረጃ እና ግብረ መልስ ለመሰብሰብ ያቀዱ አጋሮችን እንፈልጋለን። ለመማር እና ማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን ለማድረግ ቁርጠኛ የሆኑ ተግባራት ከፕሮግራማችን ጋር ተስማሚ ናቸው።

### 6.4. የፋይናንስ ድጋፍ መርሆዎች

ለሚከተሉት የገንዘብ ድጋፍ አንሰጥም፡-

- × የምርምር ፕሮጀክቶች
- × ለብቻቸው የሚደረጉ ጥናቶች (ለምሳሌ፡- የአዋጭነት ጥናት) ወይም ግልጽ የገቢ/የዕድገት ሞዴል የሌላቸው የካፒታል መዋዕለ ንዋይ ፍሰቶች

- × የትምህርት ድጋፎች (ለዶክትሬት፣ ለማስተርስ ወይም ለባችለር ዲግሪ)
- × አጠቃላይ የጉዞ ወጪዎች፣ የኮንፈረንስ ተሳትፎ ወይም የቀን አበል
- × የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ እና አበል
- × መሬት፣ ሕንፃ፣ የቢሮ ዕቃዎች ወይም ተሽከርካሪዎች መግዣ


### 6.5. ሚስጥራዊነት (Confidentiality)

የእርስዎን ማመልከቻ፣ እንዲሁም ማንኛውንም ተያያዥ መረጃዎችን እና ሰነዶችን በሚስጥር እንይዛለን። ይህም ከአውሮፓ ህብረት የጠቅላላ መረጃ ጥበቃ ደንብ ጋር የተጣጣመ ነው። የውጭ ገምጋሚ የእርስዎን የሥራ ዕቅድ እንዲያይ በሚደረግበት ጊዜ፣ ግለሰቡ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ ይኖርበታል። የእኛን የግላዊነት ፖሊሲ (Privacy Policy) እዚህ መመልከት ይችላሉ። here.

## ክፍል 7፡ የማመልከቻ ሂደት (Application Process)

ሁለት ደረጃዎችን የያዘ የማመልከቻ ሂደት አለን። የመጀመሪያው ደረጃ አጭር የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ (Concept Note) በድረ-ገጽ በኩል ማቅረብ ነው። ቡድናችን የእርስዎ ፅንሰ-ሀሳብ ከእኛ የገንዘብ ድጋፍ መርሃግብሮች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ይገመግማል።

ማመልከቻዎ ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ ወደ ሁለተኛው ደረጃ እንዲሸጋገሩ ጥሪ ይደረግልዎታል፤ ከዚያም ለአንዱ የድጋፍ መርሃግብር ዝርዝር ምክረ ሃሳብ (ፕሮፖዛል) እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ምክረ ሃሳብዎ በቡድናችን እና (አንዳንድ ጊዜ) በውጭ ገምጋሚዎች ይመረመራል፤ ይህም የበይነመረብ ቃለ-መጠይቆችን እና በርካታ የግብረ-መልስ (Feedback) ዙሮችን ሊያካትት ይችላል።




### ደረጃ 1፡ የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ (Concept Note)

1. አመልካች የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫውን በኢንተርኔት (Online) ያቀርባል።

2. ቡድናችን የብቁነት ማጣሪያ ያካሂዳል።
3. አመልካች ወደ ደረጃ 2 እንዲሸጋገር ጥሪ ይደረግለታል።

### ደረጃ 2፡ የምክረ ሃሳብ/ፕሮፖዛል ማዋቀር (Proposal / Structuring)

1. በዋናው አመልካች ላይ ተገቢው የማጣራት ሥራ ይከናወናል።
2. **በስኬት ምዕራፍ ላይ ለተመሰረቱ ድጋፎች/ቴክኒክ ድጋፍ፡-** አመልካች ሙሉ የሥራ ዕቅድ ያቀርባል።
3. **በውጤት ላይ ለተመሰረቱ ድጋፎች፡-** አመልካቹ እና 'አኳ ፎር አል' በጋራ የሥራ ዕቅዱን ያዘጋጃሉ።

### ልብ ይበሉ፡

> 1. ሁሉም ማመልከቻዎች የእኛን የመስመር ላይ የማስረከቢያ ስርዓት በመጠቀም መቅረብ አለባቸው። ማንኛውንም ማመልከቻ በኢሜል አንቀበልም።
>
> 2. የአኳ ፎር አል የስራ ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው። ሁሉም የፅንሰ-ሀሳብ ማስታወሻዎች እና ሀሳቦች በእንግሊዝኛ መቅረብ አለባቸው። የመተግበሪያ ምላሾችን ወደ እንግሊዘኛ ለመተርጎም እገዛ ከፈለጉ እንደ ዲፕኤል (DeepL) ወይም ጉግል መተረጎሚያ (Google Translate) ትርጉም ያሉ የትርጉም መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ እንመክራለን። የትርጉም ስህተቶችን ለማስቀረት፣ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ አመልካቾች ያላቸውን የፅንሰ-ሀሳብ ማስታወሻ ወይም ምክረ ሃሳብ ተጨማሪ የፈረንሳይኛ እትም ማስገባት ይችላሉ።

### ደረጃ 1፡ አጭር የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ (Teaser Concept Note)

የእርስዎ የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ ስለ ዕቅድዎ አጭር መረጃ ለመስጠት የታለመ ነው። ይህም የእርስዎ ተነሳሽነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እና ለየትኛው የገንዘብ ድጋፍ ብቁ እንደሆኑ ለመረዳት ይረዳናል። ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ ቡድናችን ያገኝዎታል።

ወደ ሁለተኛው ደረጃ ማለፍ አለማለፍዎን ማመልከቻው ከገባበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 6 ሳምንታት ውስጥ ምላሽ ያገኛሉ።

የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ ማመልከቻውን በዎርድ (.docx) ፋይል በእንግሊዝኛ እና በፈረንሳይኛ ከ'ኤርቴብል' (Airtable) ማውረድ ይችላሉ። ይህም መረጃውን በድረ-ገጹ ላይ ከመሙላትዎ በፊት መልሶችዎን አስቀድመው እንዲያዘጋጁ ይረዳዎታል።

### ድረ-ገጽ መስመርን በመጠቀም ማመልከቻ ማቅረብ

ቅጹን በድረ-ገጹ ላይ በሚገኘው ማስፈንጠሪያ (link) በቀጥታ ማግኘት ይቻላል። አካውንት መክፈት ወይም መግባት (Login) አያስፈልግም። ቅጹ ማስፈንጠሪያው እንደተከፈተ መረጃ መሙላት መጀመር ይችላሉ።

ቅጹ ረቂቅ መረጃን ማስቀመጥ (saving drafts) ስለማይፈቅድ፣ መጀመሪያ የዎርድ ሰነዱን ከድረ-ገጹ አውርደው መልሶችዎን ከማመልከቻው ገጽ ውጭ ካዘጋጁ በኋላ ወደ ማመልከቻው ገጽ መስመር ላይ ቅጹ እንዲገለብጡ አጥብቀን እንመክራለን።

### ልብ ይበሉ፦

ቅጹን ሳይልኩ (submit ሳያደርጉ) ቢዘጉት፣ የሞሉት መረጃ ሁሉ ይጠፋል። ስለዚህ ቅጹን በአንድ ጊዜ ሞልተው ለማጠናቀቅ ዝግጁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

### ቅጹን መሙላት

ቅጹ ወደ ታች ሲወርዱ በሚታዩ ክፍሎች እና ሳጥኖች የተደራጀ ነው። በአንዳንድ ሳጥኖች ላይ ለሚሰጡት ምላሽ መሠረት ተጨማሪ ጥያቄዎች ሊመጡ ይችላሉ። የግዴታ መሞላት ያለባቸው ቦታዎች ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን፣ ማመልከቻውን ከማስገባትዎ በፊት መሞላት አለባቸው። ከማስገባትዎ በፊት ሁሉም መረጃዎች ትክክል እና የተሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

### ምላሾችዎን ማረጋገጥ

የግዴታ የሚሞላ  ቦታ ሳይሞላ ቢቀር ወይም የተሳሳተ መረጃ ቢገባበት፣ ማመልከቻውን ለማስገባት ሲሞክሩ ቅጹ ስህተት መኖሩን ያሳያል። እባክዎ እነዚያን ቦታዎች አስተካክለው ድጋሚ ያስገቡ። ሁሉም አስፈላጊ መረጃዎች በትክክል ሳይሞሉ የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫውን መላክ አይቻልም።

### ማመልከቻውን መላክ እና መረጃውን ማስቀመጥ

ቅጹን ሞልተው ሲጨርሱ በገጹ ግርጌ ያለውን 'submit' የሚለውን ይጫኑ። ካስገቡ በኋላ፦

- ✔ የማረጋገጫ መልዕክት በስክሪኑ ላይ ይታያል።
- ✔ የሞሉት መረጃ ቅጂ በቅጹ ላይ ወደሰጡት የኢሜል አድራሻ ይላክልዎታል።
- ✔ ከላይ በቀኝ በኩል ካለው የ'share' ቁልፍ አጠገብ ያለውን 'print-to-PDF' በመጠቀም ምላሾችዎን ማውረድ ወይም ማስቀመጥ ይችላሉ።

### ልብ ይበሉ፦

ይህን  ቅጽ  አንዴ ከላኩ በኋላ ተመልሰው ማስተካከል ወይም መቀጠል አይችሉም። ካስገቡ በኋላ ማስተካከያ ማድረግ ካስፈለገዎት በ programmes@aquaforall.org ማስታወሻ በመጻፍ ያግኙን።

## ደረጃ 2፡ ምክረ ሃሳብ (Proposal)

የፅንሰ-ሀሳብ መግለጫዎ ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ ለድርጅትዎ ይበልጥ ጠቃሚ ለሆነው የድጋፍ መርሃግብር ሙሉ ምክረ ሃሳብ እንዲያቀርቡ በኢሜል ጥሪ ይደረግልዎታል። በዚህ ደረጃ 'አኳ ፎር ኦል' በድርጅትዎ ላይ ዝርዝር የማጣራት ሥራ ያካሂዳል።

ለእያንዳንዱ የድጋፍ ማርሃግብር የሚቀርበው ዕቅድ እና ሂደቱ የተለያየ ስለሆነ፣ ዝርዝር መመሪያ ከጥሪ ኢሜሉ ጋር ይላክልዎታል። ይህም ፕሮጀክትዎን በሚገባ እንዲያዘጋጁ ይመራዎታል። በውጤት ላይ የተመሰረቱ መሣሪያዎች የተለመደውን የሥራ ዕቅድ ፎርማት አይከተሉም፤ ይልቁንም ከእኛ ጋር በጋራ በመሆን የሚዘጋጁ ናቸው።

የሥራ እቅዱን ካስገቡ በኋላ በመምረጫ መስፈርቶቻችን መሠረት በቡድናችን ይገመገማል። ይህ ደረጃ ቡድናችን ከእርስዎ ጋር በቅርበት በመሥራት ፕሮጀክትዎን የሚያሻሽሉ ምክሮችን እና መመሪያዎችን የሚሰጥበት ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የሥራ ዕቅድዎ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በውጭ ገምጋሚዎች ሊታይ ይችላል።

አጠቃላይ የሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት ደረጃ ላይ ያለው ሂደት ከፍተኛ መረጃ መሰብሰብን እና በእርስዎ እና በቡድናችን መካከል በርካታ የግብረ-መልስ ልውውጦችን ይጠይቃል። ይህን ሂደት ቀልጣፋ ለማድረግ፣ ከተጨባጭ እና ተለዋዋጭ የጊዜ ገደቦች ጋር አብሮ መሥራትን ይጠይቃል።

ጥያቄ ካልዎት programmes@aquaforall.org  ያግኙን ፡፡

## የቃላት መፍቻ (Glossary)

- **የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ አገልግሎቶች (Climate-Resilient Services)፡-** የአየር ንብረት አደጋዎችን መቋቋም የሚችሉ የውሃ እና ሳኒቴሽን መፍትሔዎች።
- **የጋራ የገንዘብ ድጋፍ (Co-Funding)፡-** ከአመልካቹ ወይም ከአጋሮች የሚቀርብ የገንዘብ ወይም የዓይነት አስተዋጽኦ።
- **ዕድገት ላይ ያለ ድርጅት (Growth-Stage Enterprise)፡-** የተጠቃሚዎችን ቁጥር እና ገቢን በከፍተኛ ሁኔታ በማሳደግ ላይ ያለ ድርጅት።
- **ተፅዕኖ (Impact)፡-** በአንድ ተግባር ምክንያት የሚመጣ የሚለካ ማኅበራዊ፣ አካባቢያዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ አዎንታዊ ለውጥ።
- **የተፅዕኖ ልኬት እና አመራር  (IMM)፡-** ተፅዕኖን ለመከታተል፣ ለማረጋገጥ እና ለማስተዳደር የሚያገለግል ሥርዓት።
- **የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ዝግጁነት (Investment Readiness)፡-** አንድ ድርጅት ከውጭ የመዋዕለ ንዋይ በለቤቶች የገንዘብ ድጋፍ ለመቀበል የሚያስችል የፋይናንስ እና የአመራር ብስለት ደረጃ ላይ መድረሱ።
- **ተጨማሪ ሀብት መሳብ (Leverage)፡-** የ'አኳ ፎር ኦል' ድጋፍን በመጠቀም ሌሎች የግል ወይም የመንግሥት ፋይናንሶችን ወደ ዘርፉ ማምጣት።
- **ውጤት (Outcome)፡-** በአንድ ፕሮጀክት ምክንያት በአጭር ወይም በመካከለኛ ጊዜ የሚመጣ የባህሪ፣ የእውቀት ወይም የሁኔታ ለውጥ።
- **ክንውን/ተጨባጭ ውጤት (Output)፡-** ከአንድ ፕሮጀክት ወዲያውኑ የሚገኙ ተጨባጭ ውጤቶች ወይም አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡- የሰለጠኑ ሰዎች ቁጥር)።
- **የፅንሰ-ሀሳብ ማረጋገጫ (Proof-of-Concept)፡-** አንድ ድርጅት ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በገበያ ላይ መሥራት እንደሚችል ያረጋገጠበት ደረጃ።
- **ዘላቂ ልማት ግብ 6 (SDG 6)፡-** ለሁሉም ሰው ንጹሕ ውኃ እና ሳኒቴሽንን በዘላቂነት ማዳረስ።
- **ንጹሕ የመጠጥ ውኃ አገልግሎት (Safe Drinking Water Services)፡-** ለሰው ልጅ ጤና አደገኛ ካልሆኑ ባክቴሪያዎች የጸዳ እና አስተማማኝ የውሃ አቅርቦት።
- **ደህንነቱ የተጠበቀ የጽዳት አገልግሎት (Safe Sanitation Services)፡-** የሰው ልጅ ፍሳሽ ቆሻሻን ከሰው ንክኪ በመለየት በጤናማ መንገድ የሚያስወግዱ ሥርዓቶች።
- **ማስፋፋት (Scaling)፡-** አንድን የንግድ ሞዴል ወይም መፍትሔ ጥራቱን ሳይቀንስ ወደ ብዙ አካባቢዎች እና ሰዎች የማዳረስ ሂደት።
- **ዘላቂ (Sustainable)፡-** አንድ አገልግሎት የተፈጥሮ ሀብትን ሳይበክል ለረጅም ጊዜ የመቀጠል አቅሙ።
- **የሙያዊ ድጋፍ (Technical Assistance)፡-** ንግድን ለማስፋፋት እና አደጋዎችን ለመቀነስ ለምክር አገልግሎት የሚውል ሀብት።